ኢትዮጵያዊነት፡- የዜጎች መብት ማስከበሪያ ጉባኤ

ETHIOPIAWINNET: *COUNCIL FOR THE DEFENSE OF CITIZEN RIGHTS*

*www.ethiopiawin.net*

ECDCR, P.O Box 171, East Lansing, MI 48823


# ዘረኝነትን፣ ጎሰኝነትን እናምክን፤ ለዜግነት ክብር እንታገል!

ጥቅምት 15፣ 2012 ዓ ም

ባለፉት ጥቂት ቀናት በሀገራችን፣ በተለይም በኦሮምያ ክልል የተፈጠረው ሥርዓተ አልበኝነት እስከ 67 የሚሆኑ ወገኖቻችንን ሕይወት ቀጥፏል፣ ከ 300 ያላነሱ ቆስለዋል፣ በመቶ የሚቆጠሩ ቤቶች ተቃጥለዋል፣ ግምቱ ያልታወቀ ንብረት በየከተማው ወድሟል፤ ቤተ ክርስቲያን ከአደጋው ለመጠለል የገቡ ተሳደው በቦምብ ሕይወታቸውን እንዲያጡ ሆነዋል፤ ወደ ሆስፒታል ሕይወታቸውን ከደረሰባቸው ጉዳት ለማትረፍ ሲወሰዱ  እንዳይሄዱ ታግደው ባሉበት እንዲገደሉ ተደርገዋል። ድርጅታችን **"ኢትዮያዊነት: የዜጎች መብት ማስከበርያ ጉባዔ"** የጥቃቱ ሰለባ ለሆኑ ቤተሰቦችና ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ሀዘኑን ይገልፃል።

ሀዘናችንን ይበልጥ የሚያከብደው ጥቃቱ ሆን ተብሎ ብሔርና ሃይማኖት ተኮር መሆኑ ነው። ድርጊቱ በኢትዮጵያ ለውጥ እንዲመጣ በተደረገው ሰፊ ትግል ቄሮዎችም ሆኑ ሌሎች የሀገራችን ወጣቶች ካሁን በፊት ያልሞከሩት (ታይቶ የማይታወቅ)፣ ከኦሮሞም ሆነ ከተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሥነ ልቦና ያፈነገጠ አዲስ ዓይነት የወንጀል ክስተት መሆኑም ነው።

የጉዳዩ መነሻ የአንድ ታዋቂ ግለሰብ የሚያስከትለውን መዘዝ ያላገናዘበና ቀጥተኛ የሆነ አደጋ ያልተቃጣበት የድረሱልኝ ጥሪን ተከትሎ የደረሰ ክስተት ቢሆንም፣ የዚህ ዓይነት የቡድን ጭካኔና ሥርዓተ አልበኝነት፣ በተመሳሳይ ሁኔታ፣ በብዙ ቦታዎች፣ ያለምንም መመሪያና ቅድመ ድርጅታዊ ኔትዎርክ በድንገት የሆነ ነው ለማለት እጅግ ያስቸግራል። ጉዳዩ በሂደት የሚጣራ ቢሆንም፣ በክልሉ ውስጥ ባለው የለውጡ እንቅስቃሴ ተቃዋሚዎች ሚና፣ ጥቃቱ በሚካሄድበት ጊዜ የመንግስት የፀጥታ ኃይሉ፣ በተለይም የፖሊሱ ኃይል፣ ሕግ ለማስከበር ፈቃደኛ አለመሆን፣ የወጣቶቹ አግላይ ብሔርተኝነት አስተሳሰብ(ሥነ ልቦና) የአእምሮ ቀረፃ ወዘተ፣ ሊታሰብባቸው የሚገባ ናቸው።

የዜጎችን መብት ማክበር የእያንዳንዱ ሰው ግዴታ ነው። ማንም ከሕግ በላይ አይደለም። የሰሞኑ አሳፋሪ የግፍ ድርጊት ቀደም ሲል እንደታየው በሌላ አዙሪት እንዳይደገም ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥትና የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚከተሉትን እርምጃዎች እንዲወስዱ እንጠይቃለን፣

1) መንግስት አስፈላጊውን ምርመራ አድርጎ ከሕግ ከተደነገገው ሰላማዊ ተቃውሞ የማድረግ መብት ውጭ በተለያዩ ከተሞችና አካባቢዎች በተለይ በሰው ሕይወት፣ በንብረት፣ በሃይማኖት ተቅዋማት፣ ላይ ጥፋት እንዲደርስ  ያቀዱትን፣ ያስተባበሩትን፣ ያበረታቱንና የመሩትን ለይቶ፣ በፍጥነት ለፍርድ እንዲያቀርብ።

2) የሰው ሕይወትና ንብረት ሲወድም ግዴታችውን ያልተወጡ የመንግሥት ኃላፊዎችና የፀጥታ አካላት ተጠያቂ እንዲሆኑ፣

3) ትውልድን ማነፅ የረጅም ጊዜ ሥራ ቢሆንም፣ ወጣቱ ማሕበረሰብ ላይ ያተኮረ፣ በሰብዓዊነት፣ በዜግነት መብት፣ ግዴታዎቹና በትምህርት ቤቶች፣ በኢትዮጵያዊነት ሥነ ምግባር ላይ ምክርና ትምህርት፣ በሃይማኖትና ባህል መሪዎች እንዲጀመሩ እናሳስባለን፡፡

4) ሞትና ጉዳት የደረሰባቸው ቤተሰቦች ይቅርታ እንዲጠየቁ፣ የየአካባቢያችን ባህል በሚፈቅደው መሠረት ዕርቅ እንዲወርድ፣ ለሞቱት ካሣ፤ የወደሙ የግልም ሆኑ የንግድ ተቋማት በተቻለ ካሳ እንዲከፈላቸው የሚመለከታቸው ሁሉ ጥረት ማድረግ፣ ማስተባበር፣

5) ካሁን ጀምሮ ሕዝብ ከሕዝብ ጋር እንዲጋጭ የሚሰሩ የሚድያ ተቋማት፣ የፖለቲካ መሪዎች፣ የሃይማኖት፣ የባህልና የማህበረሰብ ላይ አስተማሪ ጥብቅ እርምጃ መውሰድ፣

በመጨረሻም መላውን ኢትዮጵያዊ ወገናችን ማሳሰብ የምንፈልገው የደረሰብን ሃዘን ባለፉት 45 ዓመታት የተዛቡ ትርክቶች ውጤት መሆኑን ነው። ለመብት መታገል አንድ ነገር ነው። ወገንን በጭፍን መጥላት ሌላ ነገር ነው ። በተለይ ባለፉት 28 አመታት በተሰበከው የጎሣ ፖለቲካ ያደጉ ወጣቶች ለትርክቶቹ ሰለባ ነበሩ። ይህ የደረሰውን አደጋ ለማመክኘት ሳይሆን እውነታው ስለሆነ ነው። ያም ሆኖ ብዙ ተስፋ ያላቸው ጅምሮች አሉ፣ የለውጥ ኃይሎች በጎ የፖለቲካ እርምጃዎችን ጀምሮ። ሙሉ በሙሉ ባንስማማም በሚቻለው ልናበረታታቸው፣ ስያጠፉም ልንገስፅ ይገባል። የጎሣ ፖለቲካ አላማው አንድ ነው፣ ሥልጣን! ያለንበት ጊዜ መደጋገፍን ይጠይቃል። የበደል መብዛት ጥላቻን ይፈጥራል። ጥላቻ ግን መፍትሄ አይሆንም! ለፍትህ እንታገል፣ የተለመደው ሆደ ሰፊነት ግን አይለየን።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!